የሰ/መ/ቁ. 66210

29/11/ 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋዬ ጎላ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲስኘሊን ውሣኔ ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ይፈፀም በመባሉ ምክንያት አመልካች ይግባኛቸውን በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 29 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት አመልካችን በማሰናበት በመወሰኑ አመልካች በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን ስለአቀረቡ ነው፡፡

ለዲስኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ለተጠሪ መ/ቤት ያቀረቡት አቶ ጽጌ ጌታነህ ሲሆኑ የአቤቱታውም ፍሬ ቃሉ ከአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ ጋር በተፈጠረው ያለመግባባት ክለቡን በሕግ ፊት አመልካች አቅርበው እንዲፋረዱላቸው አመልካችን ጠይቀው አመልካችም ፈቃደኛ ሆነው የጥብቅና ሙያ ውል እንደአደረጉና አመልካች ለሚሰጧቸው አገልግሎትም ብር 2,000.00 ለመክፍል፣ አከፋፈሉም በቅድሚያ ብር 1,000.00፣ ቀሪው ብር 1,000.00 ደግሞ ጉዳዩ እንደተከናወነ እንደሚሆን ተስማምተው ቅድሚያ ክፍያውን አመልካች ተቀብለው አመልካች እንደስምምነቱ ሳይፈፅሙ ለእንግልት የዳረጓቸው መሆኑን ገልጸው የዲስፐሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸውና የተወሰደባቸው ገንዘብ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ክሱን ሊያቀርቡ ያልቻሉት አስተዳደራዊ መፍትሔዎችን ለመጨረስ ተገቢውን ሲያደረጉና ክለቡ ሕጋዊ ሰውነት ስለሌለው በፍርድ ቤት ሊከሰስ የሚችል አለመሆኑን እንዲሁም ክሱ የሚቀርበው አስተዳደራዊ መፍትሔዎች ሲያልቁ በመሆኑ በዲስፐሊን ሊያስጠይቃቸው የማይችል መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ የሥር የዲስኘሊን ኮሚቴውም የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች ሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2/ለ/ የተደነገገውን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች በመጣስ የደንበኛቸውን በአፋጣኝ

ፍትህ የማግኘት መብት ጎድተዋል፣ ይህም ሕብረተሰቡ ለሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ያለውን እምነት የሚሸረሽር ነው የሚለውን ምክንያት በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 24(3(ለ(3)) መሰረት በብር 10,000 /አሥር ሺህ/ እንዲቀጡ የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀረበ ሲሆን የበላይ ኃላፊውም የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ አጽድቀውታል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም። የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከግል ተበዳይ ጋር በተደረገው የጥብቅና ውል መሰረት ሙያው የሚጠይቀውን እየፈጸሙ ያሉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በጉዳዩ ላይ ክስ ሳያቀርቡ ዘግይተዋል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የዲስፕሊን ግድፈት ፈፅመዋል ተብሎ ብር 10,000.00 እንዲቀጡ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ተይዞ ለሰበር ችሎቱ ጉዳዩ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም አመልካች በዲሲፕሊን ግድፈት ሊጠየቁ የቻሉት ከግል ተበዳይ ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውልና ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን መፈፀማቸው በመረጋገጡ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በፅሑፍ መልሱን አቅርቧል። አመልካችም የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል።

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም አመልካች በተከሰሱበት የዲስኘሊን ክስ ጥፋተኛ ናቸው ተብለው በገንዘብ የተቀጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል።

በመሰረቱ የጥብቅና ሙያ ለእውነት፣ ለፍትህ እና ለሕግ የበላይነት መስፍን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ እሙን ሲሆን ይህንን ግብ ላይ ለማድረስ ደግሞ ሙያው ከባለሙያው የሙያ ኃላፊነቱን በታማኝነት፣ በቅንነት፣ በታታሪነትና በብቃት እንዲወጣ የሚጠይቀው ጉዳይ ይሆናል። ይህንኑ ግዴታ ያለመወጣት ደግሞ ምግባረ ብልሹነት ሲሆን ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 199/92 መግቢያው እንዲሁም አንቀጽ 30 ስር ለተመለከቱት ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 3፣8(2(ለ)) እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡና ተጠያቂነት መቼ ሊከተል እንደሚችል የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን ይዘው እናገኛለን።

ወደተያዘው ጉዳይ ሲመጣ አመልካች የዲስፕሊን ግድፈት ፈጽመዋል የተባሉት ከአቶ ጽጌ ጌታነህ ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውክልና ስልጣን መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ወስደው ጉዳያቸውን በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቅርበው ሳያስወስኑ አዘገይተዋል ተብለው ሲሆን ይህ ስለመሆኑ የዲሲፕሊን ኮሚቴው በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ጉዳዩን አስተዳደራዊ መፍትሔ እንዲሰጥበት ለማድረግ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ በማቅረብ እየተከታተሉት ያለና ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድም አቶ ጽጌ ጌታነህ እንዲከሰስላቸው የሚፈልጉት አካል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ የተቸገሩ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል። አመልካች ከአቶ ጽጌ ጌታነህ ጋር ያደረጉት የጥብቅና ውል ይዘት ሲታይም እኔ አገልግሎት ተቀባይ ከአዲስ አበባ ቴንስ ክለብ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የክለቡ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ያገደኝ በመሆኑ አገልግሎት ሰጪው አቶ ተስፋዬ ጎላ ጥሩነህ ባላቸው የጥብቅና ሙያ ከስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ጋር ተከራክረው የእኔን የክለብ አባልነት መብቴን እንዲያስጠብቁልኝ የሚል ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተረጋግጧል። አመልካች የደንበኛቸውን ጉዳይ በፍርድ ቤት ክስ ለመመስረት ያልቻሉበት ምክንያት በጉዳዩ ላይ

አስተዳደራዊ መፍትሔ ለማግኘት ነው የሚል የሚገኝበት ሲሆን ይህ ምክንያት ጉዳዩን ለመጨረስ አንዱ አካሄድ ነው ቢባልም አስተዳደራዊ መፍትሔ ለማግኘት ሲባል ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት በተገቢው ጊዜ ክስ ሳይቀርብበት እንዲቆይ የሚያደርግ አይደለም፡፡ የስር የዲስፕሊን ኮሚቴውም አስተዳደራዊ መፍትሔ መፈለግ ተገቢነቱን አምኖ አመልካችን ከተጠያቂነት ሊድኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች በትጋትና በታማኝነት ጉዳዩን ያልተከታተሉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል በማለት ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት የማስተባበያ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ሌላው አመልካች በምክንያትነት የሚያቀርቡት ነጥብ ደንበኛቸው እንዲከሰስ የሚፈልጉት አካል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ምክንያት ጠበቃው የሙያው ስነ ምግባሩን መሰረት በማድረግ በሙያው ሕጋዊ ነው የሚለውን አስተያየት የማቅረብ ሙያዊ ነፃነት ያለው መሆኑ ቢታወቅም ይህንኑ ነፃነቱን ደግሞ የደንበኛውን ፍላጎት ማዕከል በአደረገ መልኩ ሊወጣው የሚገባው ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ደንበኛቸው እንዲከሰስ የሚፈልጉትን አካል ከሰው ይኸው አካል የሕግ ሰውነት ያለው መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ማድረግ የሚችሉት ነጥብ በመሆኑ ክስ ላለማቅረብ እንደ በቂ ሕጋዊና ሙያዊ ምክንያት ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ከደንበኛቸው ጋር ያደረጉት የጥብቅና ውክልና ስልጣን ሰነድ ይዘቱ ሲታይ አመልካች ክሱን በተገቢው ጊዜ በፍርድ ቤት እንዲያቀርቡና የደንበኛቸውን መብት እንዲያስጠብቁ ግዴታ የሚጥልባቸው መሆኑና አመልካች ይህንኑ ግዴታቸውን በተገቢው ጊዜና በትጋት ሳይወጡ ቀርተው ጉዳዩን ያዘገዩ መሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዲስፕሊን ኮሚቴውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተስማሙት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋጋጠው ነጥብ ከላይ የተጠቀሰው ከሆነ አመልካች በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(2(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24(3(ለ-3)) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ ተብለው በብር 10,000.00(አስር ሺህ) መቀጣታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ